# Ethiopian Journal of Business and Social Science

**Available online at:** https://survey.amu.edu.et/ojs/index.php/EJBSS/issue/archive

**Volume: 4 Number: 2 , 2021 , Pages: 36~50**

**ISSN:2707-2770**


# በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የማንበብ ግለብቃት እምነት ተዛምዶ፡ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ተተኳሪነት


**ይድነቃቸው ገረመው* ገረመው ለሙ ** ሰይድ ይመር*****



***Article Info***

*Accepted on October, 2021*

*Received in revised form: November,2021*

*Published on: December, 2021*



***©Arba Minch University, all rights reserved***



## *አህጽሮተጥናት*

በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ግለብቃት እምነት መካከል ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ነው፡ ፡ የተዛምዶ ፍተሻውን ለማድረግ ጥናቱ ተዛምዷዊ የምርምር ንድፍን ተከትሎ ተከናውኗል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በአዲስ አበባ አስተዳደር በሁለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የአማርኛ ቋንቋ አፍፊት የሆኑ የ2013 የትምህርት ዘመን የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ የተሳታፊዎቹ አመራረጥ እኩል እድል ሰጭ ንሞና ዘዴ በመጠቀም ተከናውኗል፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተናና የማንበብ ግለብቃት እምነት መጠይቅ በመጠቀም ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃ ከተጠናቀሩ በኋላ ገላጭ ስታትስቲክሳዊ ዘዴዎችን በመጠቀም ለጥናቱ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት የሚያስችል የመረጃ ትንተና ተካሂዷል፡፡ ከመረጃ ትንተናው የተገኘው ውጤት (56.65%) የአብዛኞቹ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከለኛ እንደሆነ አሳይቷል፡፡ የተማሪዎቹ የማንበብ ግለብቃት እምነት አማካይ ውጤት (3.9) ከመካከለኛ በላይ መሆኑንም ከጥናቱ መረዳት ተችሏል፡፡ በተላውጦዎቹ መካከል ተዛምዶ መኖሩን ለመፈተሽ በተካሄደ የፒርሰን ተዛምዶ ትንተና መሰረት በአስራ አንደኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና በማንበብ ግለብቃት እምነት መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ መኖሩን የጥናቱ ውጤት (r=.263) አሳይቷል፡፡ በጥናቱ ውጤት መነሻነት የተማሪዎችን የማንበብ ግለብቃት እምነት ማሳደግ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ሊያዳብር ስለሚችል በመማር ማስተማር ሂደት ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡



**ቁልፍ ቃላት፡** አንብቦ የመረዳት ችሎታ፣ የማንበብ ግለብቃት እምነት፣ አማርኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች፣ የማንበብ ግለብቃት እምነት ምንጮች


1


* ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ስልክ፡ 0911448953 ኢሜይል፡ yidnekachew100@gmail.com

** አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

*** መቀለ ዩኒቨርሲቲ፣ መቀለ፣ ኢትዮጵያ

**የጥናቱ ዳራ**

አንብቦ የመረዳት ችሎታ በትምህርት ቤት ብቻ ሳይገደብ በተማሪዎች የህይወት ዘመን የሚኖረው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ የማንበብ ክሂል ትምህርት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የሚያዳብር መሆን ተማሪዎችን ዘለቄታዊ ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል፡፡ የቋንቋ ትምህርት ብሎም የአንብቦ መረዳት ትምህርት ውጤታማ እንዲሆን የመማር ማስተማር ሂደቱ ተማሪዎች ሃላፊነት ወስደው የራሳቸውን የመማር ሂደት እንዲመሩ የሚያበቃቸው እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ ተማሪዎች የመማር ተግባራቸውን በሃላፊነት እንዲያከናውኑ ደግሞ የማንበብ ግለብቃት እምነታቸው ወሳኝነት ይኖረዋል (Schunk, 2003)፡፡

የግለብቃት እምነት አንድ ሰው [ተማሪ] የተወሰኑ ድርጊቶችን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ክሂሎችን በመጠቀም ተግባራትን አቀናጅቶ የመተግበር ችሎታውን በተመለከተ የሚኖረው የራስ ግምት ነው (Zimmerman, 1989, p. 329)፡፡ የግለብቃት እምነት በአጭሩ አንድ ሰው አንድን ድርጊት ለመፈጸም ስላለው ችሎታ የሚኖረው ግምት ነው፡፡ አዎንታዊና የዳበረ የግለብቃት እምነት አካባቢን ተቆጣጥሮ በማመቻቸት ተግባራትን በማከናወን የተፈለገውን ውጤት ለማምጣት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል (Bandura, 1997)፡፡

አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማህበረሰብ ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ አስፈላጊ በመሆኑ ተማሪዎች ይህን ክሂል የሚማሩበት መንገድ በራስ ተነሳሽነት አንባቢ እንዲሆኑ የሚያስችላቸው እንዲሆን ይጠበቃል (Van den Broek, Rapp & Kendeou 2005)፡፡ ‹‹አንብቦ የመረዳት ችሎታ በጣም አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም፥ ተማሪዎች በሁሉም ትምህርቶች በማንበብ እንዲማሩ ብቁ ያደርጋል፡፡ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው የሚያነቡ… እንዲሆኑ ያስችላል፤ ከዚህም በላይ በህይወት ዘመናቸው ለመማርና ከተለያዩ ምንጮች መረጃ ለማግኘት ክሂሉን ይጠቀሙበታል›› (የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር፣ 2007 ዓ.ም. ገጽ 6)፡፡

ስለሆነም ከቀደሙት የክፍል ደረጃዎች የበዙ እና የከበዱ ትምህርታዊ ተግባራትን ማከናወን የሚጠበቅባቸው የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የመማር ሂደታቸውን የሚቆጣጠሩ እና የሚመሩ መሆን ይኖርባቸዋል (Nilson, 2013)፡፡ ይህ ደግሞ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ተማሪዎች አዎንታዊ የግለብቃት እምነት ሲኖራቸው ነው (Bandura, 1997)፡፡ ተማሪዎች ቋንቋ ሲማሩ ደግሞ የበለጠ በአዎንታዊ የግለብቃት እምነት ላይ የተመሰረቱ የመማር ብልሃቶች ተጠቅመው የማንበብ ተግባራቸውን የሚያቅዱ፣ የሚቆጣጠሩ እና የሚገመግሙ ከሆነ ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ (Schunk, 2003)፡፡

በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል ተማሪዎች የማንበብ ክሂል በተለይ ደግሞ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው (Piper, 2010) ፡፡ ከዚህ ጥናት ቀደም ብለው የተሰሩ የማስተዋል (1989 ዓ.ም.)፣ የተስፋዬ (2001 ዓ.ም.) እና የSileshi (2007) ጥናቶችም እንዲሁ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አረጋግጠዋል፡፡ የዚህ ጥናት ዓላማ ደግሞ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ግለብቃት እምነታቸው ያላቸውን ተዛምዶ ማጥናት ነው፡፡

**የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት**

በኢትዮጵያ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ጀምሮ የአፍመፍቻ ቋንቋ፣ አማርኛ እና እንግሊዝኛ እያንዳንዳቸው እንደ አንድ የትምህርት አይነት ይሰጣሉ፤ እንደየአካባቢው ሁኔታ ከአንደኛ እስከ አምስተኛ ካሉ ክፍሎች ጀምሮ አማርኛ እንደ አንድ የትምህርት አይነት

ይሰጣል፡፡ ይሁን እንጂ በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች የሚገኙ ተማሪዎች በእንግሊዝኛም ሆነ በአማርኛ አንብቦ ለመረዳት እና ለመግባባት ይቸገራሉ (Alidou, 2007; Berhanu, Heugh, Benson & Mekonnen, 2009; Piper, 2010)፡፡ አንብቦ መረዳት ደግሞ ለትምህርታዊና ተግባቦታዊ ችሎታ ማደግ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት ስለሚታመን (Cekiso, 2012; Krashen, 2004; Menaka & Jebaraj, 2017) የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከማንበብ ግለብቃት እምነት ጋር ያለውን ተዛምዶ በተለየ ማጥናት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በግለብቃት እምነት እና በተማሪዎች ውጤታማነት መካከል ተዛምዶ እንዳለ የሚያሳይ ውጤት ማግኘታቸውን የተለያዩ ጥናቶች (Bandura, Barbaranelli, Caprara & Pastorelli, 1996; Zimmerman, 1990) ገልጸዋል፡፡ ከቋንቋ ትምህርት ጋር በተያያዘ ከተጠኑ ዓለም አቀፍ ጥናቶች ውስጥም Lynch (2002); Piercey (2013); Sardareh, Saad & Boroomand (2012); Schunk (2003) & Tobing (2013) የግለብቃት እምነት ከተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ጋር አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳለው በጥናቶቻቸው አሳይተዋል፡፡

ይሁንና በተቃራኒው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከግለብቃት እምነት ጋር ግንኙነት እንደሌለው ያመላከቱ ጥናቶችም አሉ፡፡ ለምሳሌ በCarroll & Fox (2017) ጥናት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሴት እና ወንድ ተማሪዎች የግለብቃት እምነት እና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸው ተዛምዶ ተመርምሮ በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል ተዛምዶ አለመኖሩ ተገልጿል፡፡ የOden, Ebuta & Nta, (2012) ጥናትም በተመሳሳይ በተማሪዎች የግለብቃት እምነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ተዛምዶ እንደሌለ አሳይቷል፡፡ በአጠቃላይ በአንብቦ መረዳት ችሎታና የግለብቃት እምነት መካከል ተዛምዶ መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ የተካሄዱት ጥናቶች ውጤት ላይ የታዩት መለያየቶች ወይም ክፍተቶች ጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ጥናት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ያመለክታሉ፡፡

የግለብቃት እምነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ በተለይም በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ ከመረዳት ችሎታ ጋር ያላቸውን ተዛምዶ በተመለከተ ደግሞ ለዚህ ጥናት በተደረገ ፍተሻ ምንም ጥናት ማግኘት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ይህን ጥናት ለማድረግ ሌላኛው ምክንያት የሆነው ከዚህ ርዕስ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ያላቸው ጥናቶች ባለመካሄዳቸው በሀገራችን አውድ በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከማንበብ ግለብቃት እምነት ጋር ያለውን ግንኙነት ለመመርመር ነው፡፡

በአጠቃላይ የዚህን ጥናት ተላውጦዎች ተዛምዶ ለመፈተሽ የተካሄዱ ጥናቶች አዎንታዊና አሉታዊ የተዛምዶ ውጤት ማግኘታቸው፤ እንዲሁም በኢትዮጵያ በተለይም በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የግለብቃት እምነት ተዛምዶ አለመጠናቱ ይህን ጥናት ለማድረግ አነሳሽ ምክንያቶች ሆነዋል፡፡ የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የ11ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ደረጃ ላይ ነው?
- የ11ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች የማንበብ ግለብቃት እምነት ምን ደረጃ ላይ ነው?
- በ11ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ግለብቃት እምነት መካከል ተዛምዶ አለ?

**የአጠናን ዘዴ**

*የዚህ ምርምር ዓላማ በተማሪዎች የማንበብ ግለብቃት እምነት እና በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ መመርመር በመሆኑ ጥናቱ ተዛምዷዊ የምርምር ንድፍን የተከተለ ነው፡፡ ለዚሁ ዓላማ በምርምሩ የተሰበሰበው መረጃ በአሃዛዊ መንገድ የቀረበ በመሆኑ ይህ ምርምር በአይነቱ መጠናዊ ምርምር ነው፡፡*

**የጥናቱ ተሳታፊዎች**

*ጥናቱ በአማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች ላይ ያተኮረ ሲሆን ለዚህም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች በጥናቱ እንዲሳተፉ ተመርጠዋል፡፡ በከተማው ከሚገኙ ክፍለከተሞች ውስጥ እኩል አድል ሰጭ በሆነው በተራ የእጣ ንሞና ዘዴ የካ ክፍለከተማ ተወስዷል፡፡ በማስከተል በየካ ክፍለከተማ ውስጥ ከሚገኙ ዘጠኝ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተራ የእጣ ንሞና ዘዴ በመጠቀም ሁለት ትምህርት ቤቶች (ደጃዝማች ወንድይራድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና የካ አባዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) ተመርጠዋል፡፡*

*የዚህ ተዛምዷዊ ጥናት ተሳታፊዎች የአስራአንደኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ ተማሪዎቹ ለዚህ ጥናት የተመረጡበት ምክንያት በዚህ ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች ያላቸው የእድሜ እና የትምህርት ዝግጅት በራስ ተነሳሽነት እያነበቡ እንዲማሩ ስለሚያደርጋቸውና ስርዓተ-ትምህርቱም ይህን ስለሚጠብቅባቸው ነው፡፡ በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ ካሉ የአስራአንደኛ ክፍል ምድቦች ውስጥ ተራ የእጣ ንሞና ዘዴ በመጠቀም ከያንዳንዱ ሁለት በድምሩ አራት ምድቦች በናሙናነት ተመርጠዋል፡፡ በናሙናነት በተመረጡት አራት ምድቦች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች በሙሉ የጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ከእነዚህ ምድቦች የተገኙ ተማሪዎች ብዛትም በድምሩ ሁለት መቶ ሶስት ተማሪዎች ሆኗል፡፡*

***የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች***

*ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሁለት አይነት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ እነዚህ የጥናቱን ተላውጦዎች ለመለካት ተግባር ላይ የዋሉት መሳሪያዎች የጽሁፍ መጠይቅና ፈተና ናቸው፡፡*

**የማንበብ ግለብቃት እምነት መጠይቅ**

*ይህ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ተማሪዎች ስለራሳቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸውን ግምት ለመለካት ያገለገለ የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡ ለዚህ ዓላማ በ*Henk, Marinak & Melnick (2012) *የተዘጋጀው የማንበብ ግለብቃት እምነት መጠይቅ* (the Reader Self-Perception Scale 2 (RSPS 2)) *ተመራጭ ሆኗል፡፡ መጠይቁ የሊከርት ክፍል ን በመጠቀም የተዘጋጀ ሲሆን የመጠይቁ ጥያቄዎችም፤ ከበጣም እስማማለሁ* (5) *እስከ በፍጹም አልስማማም* (1) *ድረስ ያሉ የስምምነትን ደረጃ የሚገልጹ ባለ አምስት ክፍል አማራጭ መልሶች የያዙ ናቸው፡፡*

*መጠይቁ አርባ ሰባት ጥያቄዎች የነበሩት ሲሆን መረጃ ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት በጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የማስተማር እና የምርምር ልምድ ካላቸው የአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነዘዴ ምሁራንና ከትምህርታዊ ስነልቦና ምሁራን ጋር በመነጋገር*

ከተግባራዊ ሁኔታዎች አንጻር (ለምሳሌ ከባህል አንጻር ተገቢነትን ለመፍጠር፣ አላስፈላጊ ተመሳሳይነት ያላቸውን ጥያቄዎች ለማስቀረት፣ የተማሪዎችን መሰላቸት ለመቀነስ) ከየንዑስ ክፍሎቹ ተደጋጋሚነት ያላቸውን ጥያቄዎች በጥንቃቄ በመቀነስ የመጠይቁ ጥያቄዎች ሃያ ሶስት እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ በዚህ መጠይቅ ውስጥ ያሉ በተገላቢጦሽ የቀረቡ ጥያቄዎች ምላሾቻቸው በተገላቢጦሽ ተመዝግቧል፡፡ በHenk, Marinak & Melnick (2012) የተዘጋጀው መጠይቅ አራት ንዑስ ክፍሎች አስተማማኝነት በክሮንባኽ አልፋ ተለክቶ አማካዩ .92፣ መሆኑ በአዘጋጆቹ ተገልጿል፡፡ በዚህ ጥናትም በክሮንባኽ አልፋ ተለክቶ የተገኘው የመጠይቁ አስተማማኝነት .848 ሲሆን ይህም ከ0.7 በላይ በመሆኑ የመጠይቁ የአስተማማኝነት ደረጃ ጥሩ መሆኑን ያመለክታል፡፡

**የችሎታ መለኪያ ፈተና**

በዚህ ጥናት የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ የተለካው ለዚሁ ጥናት ተብሎ በተዘጋጀ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ነው፡፡ ይህ ፈተና አንብቦ በግልጽ የቀረበ ሀሳብን የመረዳት ችሎታ፣ አንድምታዊ ፍቺን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና አንብቦ አውዳዊ ፍቺን የመረዳት ችሎታን ለመፈተሽ በሚያስችል መልኩ መሰረታዊ የፈተና ባህሪያትን ተከትሎ ተዘጋጅቷል፡፡

የተዘጋጀው ፈተና አንድ ምንባብ እና ሃያ ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን በምሁራን እና ተፈታኞቹን ተማሪዎች በሚያስተምሩ የአስራአንደኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተገቢነቱ ተገምግሞ አስተያየት እንዲሰጥበት ከተደረገ በሁዋላ በተሰጡት አስተያየቶች መሰረት ተስተካክሎ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ይህ የችሎታ መለኪያ ፈተና አስተማማኝነቱ በክሮንባኽ አልፋ ተለክቶ .825 በመሆኑና ይህም ከ0.7 በላይ በመሆኑ የፈተናው የአስተማማኝነት ደረጃ ጥሩ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

እነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተግባራዊ ከመሆናቸው በፊት በናሙናነት በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ምርምሩን ለማድረግ የሚያስችል ፈቃድ ለማግኘት ጥያቄ ለትምህርት ቤቶቹ አስተዳደር ቀርቦ ፈቃድ ተገኝቷል፡፡ በመረጃ አሰባሰብ ሂደት የሚሳተፉ መምህራን የጥናቱ ኣላማ ከተገለጸላቸው በኋላ የተሳትፎ ፈቃዳቸውን ተጠይቀው አዎንታዊ ምላሽ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች አስተማሪዎቻቸው በተገኙበት ስለጥናቱ ዓላማ ማብራሪያ ተሰጥቷቸው የተሳትፎ ፈቃዳቸው ከተገኘ በኋላ መጠይቁን በመሙላትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተናውን በመስራት በጥናቱ ተሳትፈዋል፡፡

**የመረጃ አተናተን**

የጥናቱ ዋና ዓላማ በተማሪዎች የማንበብ ግለብቃት እምነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ በመሆኑ በፈተና እና የጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በገላጭ የስታትስቲክስ ዘዴዎች ተተንትነዋል፡፡ በፈተና የተሰበሰቡ መረጃዎችን ገላጭ ስታትስቲክስ በመጠቀም የጥናቱን ተሳታፊዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በሚገልጹ አማካዮች እና መደበኛ ልይይቶች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

ከጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ውስጥ የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን ለመመለስ የጥናቱ ተሳታፊዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና ውጤት እንዲሁም የማንበብ ግለብቃት እምነት ውጤት አማካይና መደበኛ ልይይት ትንተና ተደርጓል፡፡ በማስከተል በጥናቱ ተላውጦዎች መካከል ስላለው ተዛምዶ ለተሰነዘረው የጥናቱ ሶስተኛ ጥያቄ መልስ ለማግኘት የፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት ኮሪሌሽን

ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በአጠቃላይ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ ከናሙና ተማሪዎች የተሰበሰቡትና የተጠናቀሩት መረጃዎች SPSS በመጠቀም ተተንትነዋል፤ ውጤቶቹም ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

**የውጤት ትንተና**

ከጥናቱ አካላይ የተወሰዱት ተሳታፊዎች 203 ሲሆኑ ከጾታ አንጻር 137ቱ ሴቶች 66ቱ ደግሞ ወንዶች ናቸው፡፡ ይኸውም በመቶኛ ሲገለጽ ሴቶች 67.5 በመቶ፤ ወንዶች 32.5 በመቶ ናቸው፡፡ የውጤት ትንተናው የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ ቀርቧል፡፡

የተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያለበትን ደረጃ ለመወሰን የፈተና ውጤት አማካይና መደበኛ ልይይት ተፈትሿል፡፡ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል ለሚለው ጥያቄ መልስ ለማግኘት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተናው የተገኘው ውጤት ትንተና በሰንጠረዥና በገለጻ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 1** *የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ አማካይና መደበኛ ልይይት*

| ጥገኛ ተላውጠ | አማካይ* | መደበኛ ልይይት | አንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 0-25 | 26-49 | 50-75 | 76-100 |
| 1. አንብቦ በግልጽ የቀረበን ሀሳብ የመረዳት ችሎታ | 49.81 | 22.91 | 45 (22.2%) | 39 (19.2%) | 81 (39.9%) | 38 (18.7%) |
| 2. አንብቦ አንድምታዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ | 59.41 | 27.93 | 35 (17.2%) | 38 (18.7%) | 45 (22.2%) | 85 (41.9%) |
| 3. አንብቦ አውዳዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ | 64.46 | 30.80 | 30 (14.8%) | 16 (7.9%) | 59 (29%) | 98 (48.3%) |
| 4. አንብቦ የመረዳት ክሂል | 56.65 | 22.46 | 32 (15.7%) | 36 (17.7%) | 98 (48.3%) | 37 (18.3%) |

*ናሙና=203

በሰንጠረዥ 1 የቀረበው መረጃ በግልጽ የቀረበን ሀሳብ አንብቦ የመረዳት ችሎታ፣ አንድምታዊ ፍቺን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና አውዳዊ ፍቺን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የሚሉ አንብቦ የመረዳት ክፍሎች ላይ የተማሪዎቹ የችሎታ አማካይ እና የተማሪዎች ስርጭት በችሎታ አማካይ መለኪያ ምን እንደሚመስል የሚያስረዳ ነው፡፡ በሰንጠረዡ መረጃ መሰረት የተማሪዎቹ የችሎታ አማካይ በአንብቦ መረዳት ክፍሎች ሲገለጽ በግልጽ የቀረበን ሀሳብ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አማካይ 49.81%፣ አንድምታዊ ፍቺን አንብቦ የመረዳት ችሎታ አማካይ 59.41% እና አውዳዊ ፍቺን አንብቦ የመረዳት ችሎታ አማካይ 64.46% መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ አንብቦ የመረዳት ክፍሎች ድምር ውጤት የሆነው የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ አማካይ 56.65% መሆኑን የሰንጠረዡ መረጃ ያመለክታል፡፡

ሰንጠረዥ 1 ከችሎታ አማካይ በተጨማሪ የተማሪዎች ስርጭት በችሎታ አማካይ መለኪያ በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ የሚያሳይ መረጃ ይዟል፡፡ በመረጃው መሰረት የአንብቦ መረዳት ፈተናውን ከተፈተኑ ተማሪዎች መካከል በግልጽ የቀረበን ሀሳብ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ክፍል ከ76%-100% ውጤት ያገኙ ተፈታኞች 38(18.7%)፣ ከ50%-75% ውጤት ያገኙ ተፈታኞች 81

(39.9%) እና ከ50% በታች ውጤት ያገኙ ተፈታኞች 84 (41.4%) ናቸው፡፡ አንድምታዊ ፍቺን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ክፍልን በተመለከተ ከ76%-100% ውጤት ያገኙ ተፈታኞች 85 (41.9%)፣ ከ50%-75% ውጤት ያገኙ ተፈታኞች 45 (22.2%) እና ከ50% በታች ውጤት ያገኙ ተፈታኞች 73 (35.9%) ሲሆኑ አውዳዊ ፍቺን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ክፍልን በተመለከተ ደግሞ ከ76%-100% ውጤት ያገኙ ተፈታኞች 98 (48.3%)፣ ከ50%-75% ውጤት ያገኙ ተፈታኞች 59 (29%) እና ከ50% በታች ውጤት ያገኙ ተፈታኞች 46 (22.7%) መሆናቸውን ከሰንጠረዡ መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡

የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናው አጠቃላይ ውጤት እንደሚያሳየውም ከ50% በታች ውጤት ያገኙ ተፈታኞች 68 (33.4%) ሲሆኑ፤ ከ50%-75% ውጤት ያገኙ ተፈታኞች 98 (48.3%) ፣ ከ75%-100% ውጤት ያገኙ ተፈታኞች ደግሞ 37 (18.3%) ናቸው፡፡ ከዚህም አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተናውን የተፈተኑ የተማሪዎች ውጤት መካከለኛ የሚባል እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የ11ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንደሆነ ለሚጠይቀው የጥናቱ ጥያቄ የፈተናው አማካይ ውጤት (56.65%) እና የውጤት ስርጭቱ አብዛኞቹ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው አማካይ (መካከለኛ) እንደሆነ ያሳያል፡፡

ስለሌላኛው የጥናቱ ተላውጦ የማንበብ ግለብቃት እምነት ከጥናቱ ተሳታፊዎች የተሰበሰበው መረጃ አማካይና መደበኛ ልይይት በቀጣዩ ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 2** *የተማሪዎች የማንበብ ግለብቃት እምነት ምላሽ አማካይና መደበኛ ልይይት*

| የመጠይቅ ክፍሎች | የአማካዮች አማካይ* | የድምር አማካይ** | የድምር አማካይ መደበኛ ልይይት |
|---|---|---|---|
| የራስ ለውጥ(Progress) ግለብቃታዊ ምንጮችን በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተማሪዎች ምላሽ | 4.47 | 29.03 | 4.10 |
| ምልከታዊ ንጽጽር (Observational Comparison) ግለብቃታዊ ምንጮችን በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተማሪዎች ምላሽ | 3.51 | 17.57 | 3.13 |
| ምጋቤምላሽ (Social Feedback) ግለብቃታዊ ምንጮችን በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተማሪዎች ምላሽ | 3.28 | 16.41 | 3.15 |
| ስሜታዊ ሁኔታ (Physiological States) ግለብቃታዊ ምንጮችን በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተማሪዎች ምላሽ | 4.09 | 20.45 | 3.71 |
| የግለብቃት እምነትን ለመፈተሽ ለቀረበ ጥቅል ጥያቄ የተማሪዎች ምላሽ | 3.93 | - | 0.82 |

የጥናቱን ተሳታፊዎች የንባብ ግለብቃት እምነት በተመለከተ መረጃ ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ የዋለው የጽሁፍ መጠይቅ በአራት ክፍሎች የተከፋፈሉ ሃያሶስት ጥያቄዎች ያሉት ነው፡፡ ተሳታፊዎቹ ለእነዚህ ክፍሎች የሰጡት ምላሽ አማካይና መደበኛ ልይይት በሰንጠረዥ 2 የቀረበው ነው፡፡ በሰንጠረዡ መረጃ መሰረት የራስለውጥ ግለብቃታዊ ምንጭ ክፍል ከፍተኛ (29.03) አማካይ የተመዘገበበት ክፍል ሆኗል፡፡ በ20.45 አማካይ የሁለተኛነቱን ደረጃ የያዘው የስሜታዊ ሁኔታ ግለብቃታዊ ምንጭ ክፍል ሲሆን የምልከታዊ ንጽጽር

ግለብቃታዊ ምንጭ ክፍልና የምጋቤምላሽ ግለብቃታዊ ምንጭ ክፍል ደግሞ በቅደምተከተል 17.57 እና 16.41 አማካይ ውጤት የተመዘገበባቸው ክፍሎች ናቸው፡፡

ከአራቱ የማንበብ ግለብቃት እምነት ክፍሎች ውስጥ የራስለውጥ ግለብቃታዊ ምንጭ ክፍል ብቻ ሰባት ጥያቄዎች ያሉት ሲሆን የተቀሩት ክፍሎች እያንዳንዳቸው አምስት አምስት ጥያቄዎች ያሏቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም የክፍሎቹ የድምር አማካይ ሲነጻጸር ከጥያቄዎቻቸው ብዛት አንጻር መሆን ስላለበት የራስለውጥ ግለብቃታዊ ምንጭ ክፍል አማካይ ከሌሎቹ ጋር ያለው ልዩነት የሰፋው ክፍሉ በጥያቄ ብዛት ከሌሎቹ በሁለት የሚበልጥ በመሆኑ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ በቀረበው የአማካዮች አማካይ ተሰልቶ የተገኘው ነጥብም (4.47) የሚያሳያው ክፍሉ ከሌሎቹ ክፍሎች የበለጠ አማካይ የተመዘገበበት መሆኑን ነው፡፡

ተማሪዎቹ ለክፍሎቹ ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ አማካይ የራስ ለውጥ የግለብቃት እምነት 4.47፣ ስሜታዊ ሁኔታ የግለብቃት እምነት 4.09፣ ምልከታዊ ንጽጽር የግለብቃት እምነት 3.51 እና ምጋቤምላሽ የግለብቃት እምነት 3.28 መሆኑን የሰንጠረዡ መረጃ ያመለክታል፡፡ በዚህ ጥናት የተገኘው አጠቃላይ የመጠይቁ ጥያቄዎች አማካይ (3.93) የተማሪዎቹ የማንበብ ግለብቃት እምነት በመካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን ያሳያል፡፡

**አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ግለብቃት እምነት ተዛምዶ**

የጥናቱ ሶስተኛ መሰረታዊ ጥያቄ *በአስራ አንደኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና በማንበብ ግለብቃት እምነት መካከል ተዛምዶ አለ?* የሚል ሲሆን መላምቱም በአስራ አንደኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና በማንበብ ግለብቃት እምነት መካከል ተዛምዶ እንደሌለ የሚገልጽ ነው፡፡ በዋናዎቹ ተላውጦዎች መካከል ያለውን ጥቅል ተዛምዶ ለመመርመር በ $P<0.05$ የስህተት ይሁንታ በባለሁለት ጫፍ ፍተሻ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመር በተደረገ የተዛምዶ ፍተሻ የተገኘው ውጤት በሰንጠረዥ 3 ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 3** *የማንበብ ግለብቃት እምነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመር*

| ተላውጦዎች | የተዛምዶ መወሰኛ ኮኦፊሸንት | |
|---|---|---|
| | 1 | 2 |
| 1. አንብቦ የመረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና አጠቃላይ ውጤት | - | $.263^{**}$ |
| 2. የማንበብ ግለብቃት እምነት መጠይቅ አጠቃላይ ውጤት | $.263^{**}$ | - |

$^{**}p<0.01$፣ ናሙና=203

በሰንጠረዥ 3 የቀረበው መረጃ የማንበብ ግለብቃት እምነት ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመወሰን በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመር ተሰልቶ የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ ነው፡፡ በሰንጠረዡ የቀረበው መረጃ በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል ጉልህ ግንኙነት መኖሩን የሚያመለክት ነው፡፡ ይኸውም በማንበብ ግለብቃት እምነት እና በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል የታየው የተዛምዶ መጠን $r=.263$ ሲሆን በተላውጦዎቹ መካከል የታየው የባህሪ ተጋርቶም 6.92% ነው፡፡ ይህ

ውጤት ስታትስቲካዊ ጉልህነት ያለው መሆኑ የሚያመለክተው በማንበብ ግለብቃት እምነትና በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ግንኙነት መኖሩን ነው፡፡ ይህም የተማሪዎች የማንበብ ግለብቃት እምነት ለተማሪዎች አንብቦ በግልጽ የቀረበን ሀሳብ የመረዳት ችሎታ፣ አንድምታዊ ፍቺን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና አውዳዊ ፍቺን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያለው አስተዋጽኦ ጉልህ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ይህ በዋና ተላውጦዎች መካከል ያለውን ተዛምዶ የሚያሳይ ሲሆን የተማሪዎች የማንበብ ግለብቃት እምነት ከአራት የግለብቃት እምነት ምንጮች አንጻር የቀረበ በመሆኑ በንዑስ ተላውጦዎች መካከል ያለው ተዛምዶ ውጤት ትንተና በቀጣይ በዝርዝር ቀርቧል፡፡ እነዚህ የማንበብ ግለብቃት እምነት ምንጮች ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያላቸውን ተዛምዶ ለመወሰን በ $P<0.05$ የስህተት ይሁንታ በባለሁለት ጫፍ ፍተሻ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመር ተሰልቶ የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ መረጃ በሰንጠረዥ 4 ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 4** *የማንበብ ግለብቃት እምነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመር*

| ተላውጦዎች | የተዛምዶ መወሰኛ ኮኦፊሸንት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 |
| 1. የራስ ለውጥ የግለብቃት እምነት ምንጮች | - | | | | | | | |
| 2. ምልከታዊ ንጽጽር የግለብቃት እምነት ምንጮች | .388** | - | | | | | | |
| 3. ምጋቤምላሽ የግለብቃት እምነት ምንጮች | .253** | .542** | - | | | | | |
| 4. ስሜታዊ ሁኔታ የግለብቃት እምነት ምንጮች | .530** | .322** | .259** | - | | | | |
| 5. አንብቦ በግልጽ የቀረበን ሀሳብ የመረዳት ችሎታ | .279** | .102 | .048 | .221** | - | | | |
| 6. አንብቦ አንድምታዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ | .336** | .157* | .003 | .215** | .571** | - | | |
| 7. አንብቦ አውዳዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ | .235** | .054 | .010 | .161* | .621** | .467** | - | |
| 8. አንብቦ የመረዳት ክሂል | .339** | .127 | .034 | .236** | .880** | .765** | .833** | - |

*p<0.05፣ **p<0.01፣ ናሙና=203

ከላይ በሰንጠረዥ 4 የቀረበው መረጃ የሚያሳየው የማንበብ ግለብቃት እምነት ከአስራ አንደኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ ነው፡፡ በሰንጠረዡ የቀረበው መረጃ በአንብቦ መረዳት ችሎታ ክፍሎች መካከል ከመካከለኛ(r=.467) እስከ ከፍተኛ (r=.880) የሚደርስ ጉልህ ተዛምዶ መኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡ በተመሳሳይ በነጻ ተላውጦዎቹ መካከል የታየው ከ r=.253** እስከ r=.542** የሚደርስ ተዛምዶ በስታትስቲክስ ጉልህ እንደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡

በሰንጠረዡ የቀረበው መረጃ በነጻና ጥገኛ ተላውጦዎቹ መካከል ያለውን ግንኙነትም የሚያሳይ ነው፡፡ ይኸውም በራስ ለውጥ የግለብቃት እምነት ምንጮች እና በተማሪዎች አንብቦ በግልጽ የቀረበን ሀሳብ የመረዳት ችሎታ፣ አንብቦ አንድምታዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ እና አንብቦ አውዳዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ መካከል የታየው የተዛምዶ መጠን በቅደምተከተል .279፣ .336፣ .235 ሲሆን በተላውጦዎቹ መካከል የታየው የባህሪ ተጋርቶም 7.78%፣ 11.29%፣ 5.52% ነው፡፡ ይኸው ተላውጦ ከአንብቦ የመረዳት ክሂል ጋር .339 የተዛምዶ መጠንና 11.49% የባህሪ ተጋርቶ መጠን አሳይቷል፡፡ ከራስ ለውጥ የሚመነጭ የግለብቃት እምነትና የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በአጠቃላይ ያሳዩት ተዛምዶ በP<0.01 የስህተት ይሁንታ ጉልህ እንደሆነ ተመላክቷል፡፡

በአንጻሩ በምልከታዊ ንጽጽር የግለብቃት እምነት ምንጮች እና በተማሪዎች አንብቦ በግልጽ የቀረበን ሀሳብ የመረዳት ችሎታ፣ አንብቦ አንድምታዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ እና አንብቦ አውዳዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ መካከል የታየው የተዛምዶ መጠን በቅደምተከተል .102፣ .157፣ .054 ሲሆን በተላውጦዎቹ መካከል የታየው የባህሪ ተጋርቶም 1.04%፣ 2.46%፣ 0.29% ነው፡፡ ይህ የሚያመለክተው ከምልከታዊ ንጽጽር በሚመነጭ የግለብቃት እምነትና በተማሪዎች አንብቦ በግልጽ የቀረበን ሀሳብ የመረዳት ችሎታ፣ አንብቦ አንድምታዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ እና አንብቦ አውዳዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ መካከል ግንኙነት አለመኖሩን ነው፡፡

በዚህ ጥናት በንባብ ግለብቃት እምነትና በአስራ አንደኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመፈተሽ በተደረገ ስታትስቲክሳዊ ስሌት የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው ከምጋቤምላሽ የሚመነጭ የማንበብ ግለብቃት እምነት ከተማሪዎች አንብቦ በግልጽ የቀረበን ሀሳብ የመረዳት ችሎታ፣ አንብቦ አንድምታዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ እና አንብቦ አውዳዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ ጋር በቅደም ተከተል .048፣ .003፣ .010 የተዛምዶ መጠን ያለው ሲሆን፤ ከእያንዳንዱ ጥገኛ ተላውጦ ጋር የተጋራው የባህሪ መጠንም 0.23%፣ 0.0009%፣ 0.01% ነው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ከምጋቤምላሽ በሚመነጭ የማንበብ ግለብቃት እምነትና በተማሪዎች አንብቦ በግልጽ የቀረበን ሀሳብ የመረዳት ችሎታ፣ አንብቦ አንድምታዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ እና አንብቦ አውዳዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ መካከል ተዛምዶ አለመኖሩን ነው፡፡ ይህም ከምጋቤምላሽ የሚመነጭ የማንበብ ግለብቃት እምነት ለተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ አስተዋጽኦ የሌለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

በሰንጠረዥ 4 የቀረበው መረጃ በተጨማሪም እንደሚያሳየው ከስሜታዊ ሁኔታ የሚመነጭ የማንበብ ግለብቃት እምነት ከተማሪዎች በግልጽ የቀረበን ሀሳብ አንብቦ የመረዳት ችሎታ፣ አንድምታዊ ፍቺን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና አውዳዊ ፍቺን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር በቅደም ተከተል .221፣ .215፣ .161 የተዛምዶ መጠን ነው ያለው፡፡ ከስሜታዊ ሁኔታ የሚመነጭ የማንበብ ግለብቃት እምነት ከእያንዳንዱ ጥገኛ ተላውጦ ጋር የተጋራው የባህሪ መጠንም 4.88%፣ 4.62%፣ 2.59% ነው፡፡ ይኸው ተላውጦ ከአንብቦ የመረዳት ክሂል ጋር .236 የተዛምዶ መጠንና 5.57% የባህሪ ተጋርቶ መጠን አሳይቷል፡፡ በመረጃው መሰረት ከስሜታዊ ሁኔታ የሚመነጭ የማንበብ ግለብቃት እምነት ከተማሪዎች አንብቦ በግልጽ የቀረበን ሀሳብ የመረዳት ችሎታና አንብቦ አንድምታዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ ጋር ያሳየው ተዛምዶ በP<0.01 የስህተት ይሁንታ፤ እንዲሁም ከተማሪዎች አንብቦ አውዳዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ ጋር ያሳየው ተዛምዶ በP<0.05 የስህተት ይሁንታ በስታትስቲክስ ጉልህ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም ከስሜታዊ ሁኔታ የሚመነጭ የማንበብ ግለብቃት እምነት ለተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ በማንበብ ግለብቃት እምነት ስር ከቀረቡት አራት ተላውጦዎች ሁለቱ ከአስራ አንደኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ተዛምዶ የሌላቸው፤ ሁለቱ ደግሞ ከአስራ አንደኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፊት ተማሪዎች

አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ተዛምዶ ያላቸው መሆኑን በሰንጠረዥ 4 ተጠቃሎ የቀረበው መረጃ ያሳያል፡፡ ከአስራ አንደኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ተዛምዶ ያላቸው ተላውጦዎች የራስ ለውጥ የግለብቃት እምነት ምንጮችና ስሜታዊ ሁኔታ የግለብቃት እምነት ምንጮች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ከአስራ አንደኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ተዛምዶ የሌላቸው ተላውጦዎች ምልከታዊ ንጽጽር የግለብቃት እምነት ምንጮችና ምጋቤምላሽ የግለብቃት እምነት ምንጮች ናቸው፡፡ ይህም የተማሪዎች የማንበብ ግለብቃት እምነት ለተማሪዎች አንብቦ በግልጽ የቀረበን ሀሳብ የመረዳት ችሎታ፣ አንብቦ አንድምታዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ እና አንብቦ አውዳዊ ፍችን የመረዳት ችሎታ ያለው አስተዋጽኦ በተወሰኑ ተላውጦዎች ጉልህ ሲሆን በተወሰኑ ተላውጦዎች ደግሞ ጉልህ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

**ማብራሪያ**

በተማሪዎች የማንበብ ግለብቃት እምነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ የጥናቱ ዋና ዓላማ በመሆኑ በችሎታ መለኪያ ፈተና እና የጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡ በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት የተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታን በተመለከተ ከቀደምት ጥናቶች (ማስተዋል፣ 1989 ዓ.ም.፤ ተስፋዬ፣ 2001 ዓ.ም.፤ Bekele, 2013; Piper, 2010; Sileshi, 2007) ውጤት ጋር ስምምነት የሌለው ሆኗል፡፡

የተማሪዎችን የማንበብ ግለብቃት እምነት በተመለከተ በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት Henk, Marinak & Melnick (2012) የሁለተኛ ደረጃ ትምርት ቤት ተማሪዎችን የማንበብ ግለብቃት እምነት አጥንተው ካገኙት ውጤት ጋር ተመሳሳይነት አሳይቷል፡፡ በዚህ ጥናት የተገኘው አጠቃላይ የመጠይቁ ጥያቄዎች አማካይ (3.93) Henk, Marinak & Melnick (2012) በጥናታቸው ካገኙት የጥያቄዎች አማካይ (3.51) ጋር ተቀራራቢነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም የተማሪዎቹ የማንበብ ግለብቃት እምነት በመካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን ያሳያል፡፡

በ11ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች የማንበብ ግለብቃት እምነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ተዛምዶ መኖሩን ለመፈተሽ በተደረገ የመረጃ ትንተና የተገኘው ውጤት በአጠቃላይ በማንበብ ግለብቃት እምነት ስር ከቀረቡት አራት ተላውጦዎች ሁለቱ ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ተዛምዶ የሌላቸው፤ ሁለቱ ደግሞ ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ተዛምዶ ያላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ የጥናቱ ውጤት የራስ ለውጥ የግለብቃት እምነት ምንጮችና ስሜታዊ ሁኔታ የግለብቃት እምነት ምንጮች ከአስራ አንደኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር በቅደም ተከተል .339** እና .236** ተዛምዶ እንዳላቸውና ምልከታዊ ንጽጽር የግለብቃት እምነት ምንጮችና ምጋቤምላሽ የግለብቃት እምነት ምንጮች ደግሞ ከአስራ አንደኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ተዛምዶ እንደሌላቸው አመልክቷል፡፡ ይህም የተማሪዎች የማንበብ ግለብቃት እምነት ለተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያለው አስተዋጽኦ በተወሰኑ ተላውጦዎች ጉልህ ሲሆን በተወሰኑ ተላውጦዎች ደግሞ ጉልህ አለመሆኑን ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ግኝት በማንበብ ግለብቃት እምነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ ካገኙ ቀደምት ጥናቶች (ሰይድ፣ 2007 ዓ.ም.፤ Lynch, 2002; Piercey, 2013; Schunk, 2003 & Tobing, 2013) ጋር ተደጋጋፊነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በአንጻሩ የዚህ ጥናት ውጤት በማንበብ ግለብቃት እምነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ተዛምዶ ካላገኙት ቀደምት ጥናቶች ውጤት (Carroll & Fox, 2017; Oden, Ebuta & Nta, 2012) ጋር ልዩነትን አሳይቷል፡፡

***መደምደሚያ አስተያየት***

በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች የማንበብ ግለብቃት እምነት እና የተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያላቸውን ተዛምዶ መፈተሽን ዋና ዓላማው ያደረገው ይህ ጥናት ‹በ11ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ግለብቃት እምነት መካከል ተዛምዶ አለ?›፣ ‹የ11ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ደረጃ ላይ ነው?› እና ‹የ11ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች የማንበብ ግለብቃት እምነት ምን ደረጃ ላይ ነው?› ለሚሉ መሰረታዊ የምርምር ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት አስችሏል፡፡

አማካይና መደበኛ ልይይት በመጠቀም በገላጭ ሰታትስቲክስ እንዲሁም ፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት ኮሪሌሽን በመጠቀም በተንባይ ስታትስቲክስ ከጥናቱ ተሳታፊዎች በአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና እና በማበብ ግለብቃት እምነት የጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበውን መረጃ በመተንተን ለምርምሩ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ተሞክሯል፡፡ በመረጃ ትንተናው ውጤት መሰረት የሚከተሉት መደምደሚዎች ላይ ተደርሷል፡፡

*‹የ11ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ደረጃ ላይ ነው?›* ለሚለው የጥናቱ ጥያቄ የፈተናው አማካይ ውጤት (56.65%) እና የውጤት ስርጭቱ አብዛኞቹ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው መካከለኛ እንደሆነ አሳይቷል፡፡ ይህም ተማሪዎቹ በአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ያስመዘገቡት ውጤት ከፍተኛ ባይሆንም አማካይ ውጤት ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል በመሆኑ በክለሳ ድርሳናት ውስጥ ከተጠቀሱት ቀደምት ጥናቶች (ማስተዋል፣ 1989 ዓ.ም.፤ ተስፋዬ፣ 2001 ዓ.ም.፤ Bekele, 2013; Piper, 2010; Sileshi 2007) ውጤት ጋር የተለየ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

*‹የ11ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች የማንበብ ግለብቃት እምነት ምን ደረጃ ላይ ነው?›* ለሚለው የጥናቱ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ተማሪዎች ለመጠይቁ ጥያቄዎች የሰጡዋቸውን ምላሾች አማካይ በመጠቀም የክፍሎች እና ጥያቄዎች አማካይ ውጤት ላይ ትንተና ተደርጓል፡፡ በውጤቱ መሰረት የተማሪዎቹ የማንበብ ግለብቃት እምነት በሶስቱ ክፍሎች ማለትም የስሜታዊ ሁኔታ የግለብቃት እምነት፣ ምልከታዊ ንጽጽር የግለብቃት እምነት እና ምጋቤምላሽ የግለብቃት እምነት መካከለኛ ደረጃ ላይ የሚቀመጥ ሲሆን የራስ ለውጥ የግለብቃት እምነት ደግሞ ከአማካይ በላይ እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል፡፡

*‹በ11ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አፍፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ግለብቃት እምነት መካከል ተዛምዶ አለ?›* ለሚለው የጥናቱ ጥያቄ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመር በመጠቀም በዋነኞቹና በንዑስ ተላውጦዎች መካከል ያለው ተዛምዶ ተፈትሾ የራስ ለውጥ የግለብቃት እምነት ምንጮች እና ስሜታዊ ሁኔታ የግለብቃት እምነት ምንጮች ከተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ክፍሎች ጋር አዎንታዊ ተዛምዶ ተገኝቷል፡፡ በአንጻሩ ምልከታዊ ንጽጽር የግለብቃት እምነት ምንጮች እና ምጋቤምላሽ የግለብቃት እምነት ምንጮች ከተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ክፍሎች ጋር ተዛምዶ የሌላቸው መሆኑን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡

በተጨማሪም በማንበብ ግለብቃት እምነት እና በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል የታየው የተዛምዶ መጠን (r=.263) ስታትስቲካዊ ጉልህነት ያለው መሆኑ የሚያመለክተው በማንበብ ግለብቃት እምነትና በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል

ግንኙነት መኖሩን ነው፡፡ ይህም የተማሪዎች የማንበብ ግለብቃት እምነት ለተማሪዎች አንብቦ በግልጽ የቀረበን ሀሳብ የመረዳት ችሎታ፣ አንድምታዊ ፍቺን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና አውዳዊ ፍቺን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያለው አስተዋጽኦ ጉልህ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

የዚህ ጥናትና የአብዛኞቹ ቀደምት ጥናቶች (ሰይድ፣ 2007ዓ.ም.፤ Lynch, 2002; Piercey, 2013; Schunk, 2003 & Tobing, 2013) ግኝት የሚያሳየው የማንበብ ግለብቃት እምነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ የሚመጋገቡ መሆናቸውን ነው፡፡ በመሆኑም መምህራን የግለብቃት እምነት መዳበር ለተማሪዎች ውጤታማነት የሚኖረውን ጠቀሜታ ሊገነዘቡ ይገባል፡፡ ተማሪዎች ስለማንበብ ግለብቃታቸው አዎንታዊ ስሜትን እንዲያዳብሩ እገዛ ቢደረግላቸው የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ሊጎለብት ይችላል፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መዳበር ደግሞ ተማሪዎች በሌሎች የትምህርት አይነቶች የሚኖራቸውን ውጤታማነት ከመጨመሩም በላይ ከትምህርት ቤት ውጭም በግላቸው ለመማር ብቁ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

በማንበብ ግለብቃት እምነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ በሌሎች የትምህርት ደረጃዎች መፈተሽ በተላውጦዎቹ መካከል ስላለው ተዛምዶ የተሟላ ግንዛቤ ለማግኘት ይረዳል፡፡ የግለብቃት እምነት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ በተጨማሪ ከሌሎች ክሂሎች ጋር ያለው ግንኙነት ቢጠና ስነትምርታዊ እና ንድፈሃሳባዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ይህን ጥናት ጨምሮ ብዙ ጥናቶች የማንበብ ግለብቃት እምነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳላቸው ቢያሳዩም በተላውጦዎቹ መካከል ተዛምዶ እንዳላገኙ የገለጹ ጥናቶችም ስላሉ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ጥናቶች ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## ዋቢዎች


ማስተዋል ውብቱ፡፡ (1989 ዓ.ም)፡፡ *የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ፤ በአዲስ አበባ በሚገኙ በአራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት* (የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፡፡

ሰይድ ይመር፡፡ (2007 ዓ.ም.)፡፡ *የአማርኛ ቋንቋ አፍፈት ሕጸናት የማንበብ አቀላጥፎሽ፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እና የማንበብ ለመዳና መማሪያ ከባቢ ተላውጦዎች ተዛምዶ (በአማራ ክልል ከደቡብ ወሎ ዞን የተመረጡ አራተኛ ክፍል ተማሪዎች)* (የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት)፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፡፡

ተስፋዬ ወልደሚካኤል፡፡ (2001 ዓ.ም.)፡፡ *የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተመረጡ የአዲስ አበባ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች* (የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር፡፡ (2007 ዓ.ም.)፡፡ *አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የመምህር መምሪያ 8ኛ ክፍል፡፡*

Alidou H. (2007). Towards quality education: The language factor. 2nd Africa Region Education Capacity Development Workshop *"Country Leadership and Implementation for Results in the EFA-FTI Partnership". Tunis.* Retrieved from http://www siteresources. worldbank. org/intafrregtopeducation/

Bandura, A. (1997). *Self-efficacy: The exercise of control.* New York: W. H. Freeman.

Bandura, A., Barbaranelli, C., Caprara, G., & Pastorelli, C. (1996). Multifaceted impact of self-efficacy beliefs on academic functioning. *Child Development, 67*(3), 1206-1222. Retrieved from http:// www.jstor.org/stable/1131888.

Bekele Birhanie. (2013). A study of self-regulated learning strategies as predictors of critical reading. *Educational Research and Reviews, 8*(21), 1961-1965.

Berhanu Bogale, Heugh, K., Benson, C., & Mekonnen Alemu. (2009). Language determination in Ethiopia: What medium of instruction? In Svein Ege, Harald Aspen, Birhanu Teferra and

Shiferaw Bekele (Eds.), *Proceedings of the 16th International Conference of Ethiopian Studies.* Trondheim. Retrieved from http://portal.svt.ntnu.no/sites/ices16/Proceedings/ Volume/204/BerhanuBogale-LanguageDeterminationinEthiopia.pdf

Carroll, J.M., & Fox, A.C. (2017). Reading self-efficacy predicts word reading but not comprehension in both girls and boys. *Frontiers in Psychology*, *7*(2056), 1-9. doi: 10.3389/fpsyg.2016.02056

Cekiso, M., (2012). Effects of strategy instruction on the reading comprehension and strategy awareness of Grade 11 English Second Language learners in the Eastern Cape. *Reading & Writing*, *3*(1), 1-8. doi:10.4102/rw. v3i1.23

Henk, W. A., Marinak, B. A., & Melnick, S. A. (2012). Measuring the reader self-perceptions of adolescents: Introducing the RSPS2. *Journal of Adolescent & Adult Literacy*, *56*(4), 311 320.

Krashen, S. D. (2004). *The power of reading: Insights from the research* (2nd ed.). Westport, Connecticut: Libraries Unlimited.

Lynch, J. (2002). Parents' self-efficacy beliefs, parents' gender, children's reader self-perceptions, reading achievement and gender. *Journal of Research in Reading*, *25* (1), 54-67. doi:10.1111/1467-9817.00158

Menaka, B. & Jebaraj J.S. (2017). Reading comprehension in relation to academic achievement in English among higher secondary students. *International Journal of Research - Granthaalayah*, *5*(5), 113- 117.

Nilson, L.B. (2013). *Creating self-regulated learners: Strategies to strengthen students' self-awareness and learning skills*. Virginia: Stylus Publishing, LLC

Oden, S. N., Ebuta, C. N., & Nta, E. G. (2012). Student's self-efficacy beliefs and their reading comprehension performance: A Nigerian perspective. *British Journal of Arts & Social Sciences*, *4*(3), 75-83.

Piercey, R. R. (2013). *Reading self-efficacy in early adolescence: Which measure works best?* (Doctoral dissertation). University of Kentucky. Retrived from https://sites.education.uky.edu/motivation/files/2013/09/Piercey_Dissertation_71813.pd

Piper, B. (2010). *Ethiopia early grade reading assessment: Data analysis report: Language and early learning*. RTI International: USAID/Ethiopia.

Sardareh, S. A., Saad, M. R., & Boroomand, R. (2012). Self-Regulated Learning Strategies (SRLS) and academic achievement in pre-university EFL learners. *California Linguistic Notes*, 37(1), 1-35.

Schunk, D. H. (2003). Self-efficacy for reading and writing: Influence of modeling, goal setting, and self evaluation. *Reading and Writing Quarterly*, 19, 159-172.Retrived from http://www.tandf.co.uk/journals/.

Sileshi Kassahun (2007). An investigation of preparatory students' reading comprehension abilities with reference to Yekatit 12 preparatory school. (Master's thesis). Addis Ababa University, Addis Ababa.

Tobing, I. (2013). The relationship of reading strategies and self-efficacy with the reading comprehension of high school students in Indonesia. (Doctoral dissertation). University of Kansas, Kansas.

Van den Broek, P., Rapp, D. N., & Kendeou, P. (2005). Integrating memory-based and constructionist processes in accounts of reading comprehension. *Discourse Processes*, *39*(2-3), 299-316.

Zimmerman, B. (1989). A social cognitive view of self-regulated academic learning. *Journal of Educational Psychology*, 81(3), 329-339.

Zimmerman, B. (1990). Self-regulated learning and academic achievement: An overview. *Educational Psychologist*, *25*(1), 3-17.